

## የተማሪ እና የቤተሰብ

# የስደተኝነት/ኢሚግሬሽን ድጋፍ

**ትምህርት ቤቶቻችን፡- ማንኛውም ልጅ—የስደተኝነት/የኢሚግሬሽን ሁኔታው(ዋ) ምንም ይሁን ምንም—መልካም አቀባበል የሚደረግበት፣ የሚከበርበት፣ እውቅና የሚሰጥበት፣እና የሚወደድበት ደህንነታቸው የተጠበቀ ቦታዎች ናቸው፤ ሆነውም ይቀጥላሉ።**

**ቁልፍ እውነታዎች፡-**

» በፌደራል ህግ መሰረት፥ ሁሉም ልጆች፣ ዜግነታቸው ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ የኮሌጅ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።

» ትምህርት ቤቶች የወላጅ ፈቃድ ሳይኖር፣ ከተማሪ ፋይል ለፌደራል የኢሚግሬሽን ወኪሎች መረጃ እንዳይሰጡ የተከለከሉ ናቸው።

» ስደተኛ ቤተሰቦች እንደሚያውቋቸው የማረጋገጥ መብት አላቸው።

## ICE ወይም ማንኛውም ከአካባቢ ውጭ የሆነ የህግ አስከባሪ አካል ወደ ትምህርት ቤት ቢመጣ ምን ይደረጋል?

ICE ወኪል ወይም ሌላ ማንኛውም ከአካባቢ ያልሆነ የሕግ አስከባሪ አካል ተማሪን/ተማሪዎችን በሚመለከት ወደ ትምህርት ቤት ከመጣ የሕንፃ አስተዳዳሪዎች መከተል ያለባቸው ጥብቅ ፕሮቶኮል አላቸው። እንደዚህ አይነት ጥያቄ ወይም ሁኔታ ሲከሰት ለቤተሰብ መግለጽ ያስፈልጋል።

## ትምህርት ቤቶች ለ ICE ወይም ሌላ ማንኛውም ከአካባቢ ውጭ የሆነ የህግ አስከባሪ አካል ስለ ቤተሰብ መረጃ ይሰጣሉ?

የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግ (FERPA)ድንጋጌ መሰረት፥የፍርድ ቤት ትእዛዝ ካልያዙ በስተቀር ትምህርት ቤቶች ለፌደራል የኢሚግሬሽን ወኪሎች ያለወላጅ ፈቃድ ከተማሪ ፋይል መረጃ እንዳይሰጡ የተከለከሉ ናቸው።

## ቤተሰቦች እንዴት መዘጋጀት ይችላሉ?

የኢሚግሬሽን ሁኔታ ስጋት ያለባቸው ቤተሰቦች ድንገተኛ ሁኔታ ለሚከሰትበት ጊዜ እቅድ ሊኖራቸው እና ልጆቻቸውን የሚንከባከብ ታማኝ የቤተሰብ አባል መሰየም አለባቸው። የድንገተኛ ጊዜ እቅድ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉ ለማወቅ እባክዎ የመጠባበቂያ ሪሶርስ መረጃውን ያንብቡ።

ስለ ህጋዊ ከለላ መረጃ

## መብቶችዎን ይረዱ

ይህ በስደተኞች ህጋዊ ከለላ ሪሶርስ ማእከል የተሰጠ የመብቶች ናሙና ካርድ ነው። የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥምዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃ ያማክሩ።

(ቆርጠው ያስቀምጡ)

| | |
|---|---|
| ሕገ መንግሥታዊ መብቶች አሉዎት፡-<br>• የኢሚግሬሽን ወኪል በር ሲያንኳኳ በሩን አይክፈቱ።<br>• የኢሚግሬሽን ወኪሎች እርስዎን ለማነጋገር ከሞከሩ ለማንኛውም ጥያቄ መልስ መስጠት የለብዎትም። ዝም የማለት መብት አለዎት።<br>• በመጀመሪያ የህግ ባለሙያ/ጠበቃ ሳያማክሩ ምንም ነገር ላይ አይፈርሙ። የህግ ባለሙያ/ጠበቃ የማናገር መብት አለዎት።<br>• ከቤትዎ ውጭ ከሆኑ፣ የኢሚግሬሽን ኤጀንቱን ለመሄድ ነፃ መሆንዎን ይጠይቁ እና አዎ ከተባሉ፣ በእርጋታ ቦታውን ለቀው ይሂዱ።<br>• ይህንን ካርድ ለኢሚግሬሽን ኤጀንቱ ይስጡ። በቤትዎ ውስጥ ከሆኑ፣ ካርዱን በመስኮት በኩል ያሳዩ ወይም በበሩ ስር ያንሸራትቱት። | በዩናይትድ ስቴትስ ሕገ መንግሥት 5ኛ የማሻሻያ አንቀጽ ባለኝ መብት መሠረት ካንተ(ቺ) ጋር ለመነጋገር፣ ለጥያቄዎችህ(ሽ) መልስ ለመስጠት፣ ወይም ማንኛውንም ሰነድ ለመስጠት አልፈልግም።<br><br>ለመግባት ከፍርድ ቤት ዳኛ ወይም ከማጅስትሬት የተፈረመበት ማዘዣ እስከሌለ ድረስ በዩናይትድ ስቴትስ ህገመንግስት 4ኛ የማሻሻያ አንቀጽ ባለኝ መብት መሰረት ወደ ቤቴ እንድትገባ(ቢ) አልፈቅድም።<br><br>4ኛው የህገመንግስት ማሻሻያ በሚፈቅድልኝ መብት መሰረት ማንኛውንም ዕቃዎቼን እንድትፈትሽ (ሺ) አልፈቅድም።<br><br>ሕገ መንግሥታዊ መብቶቼን መጠቀም ፈልጋለሁ።<br><br>እነዚህ ካርዶች ለዜጎች እና ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች ይገኛሉ። |

# የማህበረሰብ አጋሮች

## የሚከተሉት የማህበረሰብ ድርጅቶች ለቤተሰብ ድጋፍ ይሰጣሉ፡-

Gilchrist Immigrant Resource Center - ጊልክራይስት ማእከል ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ስደተኞች የሚፈልጉትን ነገር የሚያገኙበት በር ነው። ማዕከሉ በመንግስት ኤጀንሲዎች እና በማህበረሰብ ድርጅቶች ለሚሰጡ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች መረጃ እና ሪፈራል ይሰጣል። በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉላቸው፡- 240-777-4940 (www.montgomerycountymd.gov/gilchrist/immigrant-rights/)

CASA በሲልቨር ስፕሪንግ - CASA ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን በሜሪላንድ ውስጥ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ስደተኞች የህግ አገልግሎት እና ድጋፍ የሚሰጥ ድርጅት ነው። ዋናው የትኩረት መስክ በኢሚግሬሽን ህግ ዙሪያ ነው። በተለያዩ የኢሚግሬሽን ጉዳዮች፥ የዜግነት ጥያቄ ማመልከቻዎች፣ የቤተሰብ የኢሚግሬሽን አቤቱታዎች፣ የጥገኝነት እና የስደተኛነት ማመልከቻዎች፣ እና ከአገር መባረርን መከላከል የመሳሰሉ የህግ ድጋፎችን ይሰጣሉ። በዚህ የስልክ ቁጥር ይደውሉላቸው፡- 240.491.5763 (www.wearecasa.org/maryland/)

በሲልቨር ስፕሪንግ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎቶች - ናሽናል የካፒታል አካባቢ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎቶች (LSSNCA) ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን በሜሪላንድ እና በአካባቢው ሰፊ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች፥ የቤተሰብ ድጋፍ ፕሮግራሞችን እና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶችን ለምሳሌ፡- የስደተኞች መልሶ ማቋቋም እና የኢሚግሬሽን የህግ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። በዚህ ስልክ ይደውሉላቸው፡- (202) 723-3000 (www.lssnca.org)

ቤት አልባነትን የማስቆም እና የመከላከል አገልግሎት (SEPH) ፕሮግራም "Housing First philosophy" ፍልስፍና በመነሳት የቤት እጦትን መገደብ፣ ማሳነስ፣ እና በተደጋጋሚ እንዳይከሰት ለማድረግ የሚሠራ ነው። SEPH የመኖሪያ ቤት ችግርን ማረጋጋት፣ ቤት አልባነት መቅረፍ፣ እና ቋሚ የመኖሪያ ቤትን ጨምሮ ተከታታይ አገልግሎቶችን ይሰጣል። (www.montgomerycountymd.gov/homelessness/)

ቦልቲሞር የሚገኘው፥Maryland Office for Refugees and Asylees (MORA) in Baltimore, MD- MORA በፌዴራል ደረጃ እውቅና ያላቸውን የስደተኞች ማህበረሰብ አገልግሎቶችን ያስተባብራል እና ያስተዳድራል፣ የስራ አገልግሎቶችን፣ የጤና ዕርዳታዎችን፣ የወጣቶች ፕሮግራሞችን፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠናዎችን ይሰጣል። (www.dhs.maryland.gov/maryland-office-for-refugees-and-asylees/)

ዓለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ (IRC) በሲልቨር ስፕሪንግ-IRC ለስደተኞች፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች፣ ከሥቃይ የተረፉ እና ሌሎች ስደተኞች በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ እና እንዲዋሃዱ ድጋፍ ይሰጣል (www.rescue.org/united-states/silver-spring-md)

Ayuda in Silver Spring - አዩዳ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ስደተኞች ፍትህ እንዲያገኙ እና ህይወታቸውን ለመለወጥ የህግ፣ የማህበራዊ እና የቋንቋ አገልግሎቶችን ይሰጣል። (www.ayuda.com/legal-services-4/)

Immigrant & Refugee Outreach Center (IROC) በጌትስበርግ፣ MD-IROC ሞቪንግ አፕ ፈንድ "Moving Up Fund" በመሳሰሉ ፕሮግራሞች የማሰልጠን እና የማማከር እገዛን ጨምሮ ለስደተኛ ቤተሰቦች የመገልገያ ግብዓቶችን/ሪሶርሶችን ድጋፍ ይሰጣል። (www.irocenter.org/programs-for-immigrant-and-refugee-support-dmv)

ለተጨማሪ መረጃ...

